# የማንነት ፖለቲካ ጨዋታ

ግሻይ ግሸ

አሁን በሃገራችን ያለው ሁኔታ ለብዙዎቻችን ግራ የሚያጋባ ይመስላል። በተለይም በህወሃት መሪዎችና በፌደራሉ መንግስት መካከል ያለው ግንኙነት በርግጥ መንግስታዊ ሃገራዊ ወይስ የልጆች የብሽሽቅ ጨዋታ እስኪመስል ድረስ የምናያቸው ብዙ ጉዳዮች አሉ። ፌደራሊዝም ሳይገባን ነው እንዴ እጃችንን ያስገባንበት? ዲሞክራሲውስ እንደፈለጉ መዘባረቅ ነው እንዴ ? በህዝብና በህዝብ መካከል እልቂት እየደገሱ የፈለጉትን ማለት ዲሞክራሲ መገለጫው ነው እንዴ? የመንግስትን ህልውና እየሸረሸሩ በጋራ እየሰራን ነው ማለትስ ይቻላል እንዴ ? ማንነትን ያነሳ ሁሉ ካልተስተናገደ ኢዲሞክራሲያዊነት ነው እንዴ? የመደመር ፖለቲካ ከህዝብ ንቃት ጋር እንዴት ይጣጣማል ወዘተ.

ዶክተር አቢይ እንደ ሃገር መሪ ከጥቂት የለውጡ ተቃዋሚዎችና በግልጽ ከወጡትም የህወሃት መሪዎች እየተደቀነባቸው ያለውን የጦርነት ግብዣ ተቋዋቁመው እስካሁን በትእግስት የያዙት መንገድ የሚደነቅ ቢሆንም በበኩሌ የሚጎድል ነገር ያለ ይመስለኛል ። ህወሃትም ሆነ በሌሎች ድርጅቶች ውስጥ ያሉ የለውጥ እንቅፋቶችን በጅምላ እንዳናይ የጠራ መስመር ጎልቶ አለመውጣቱ ነው። ህወሃት ውስጥ ያሉ የቆዩ ፖለቲከኞች በፖለቲካ ተንኮል ረዥም ልምድ ያላቸው በመሆናቸው በወኪሎቻቸው አማካይነት በመግለጫ በንግገር በስብሰባ የሚያስተላልፉዋቸው መልእክቶች ማስረጃዎች ናቸው።

የሚጠቀሙባቸው አገላለጾች ህዝብን የሚያደናግሩ የሚከፋፍሉ ሌላው ቆርጦ እንዳይታገላቸው አብረው የቆሙ በማስመሰል ጭምር አልያም እንደተለመደው በተለይ የሚቃወሙዋቸውን ትንሽ ተንኮስ አድርገው በቀለበታቸው ውስጥ እንዲገባላቸው በማድርግ የተካኑበትን የ 27 አመት ፖለቲካ ዛሬም እየተጫወቱበት ነው። ህወሃት ኢሃዴግ ሃያ ሰባት አመት የቆየበት ሚስጥር ሌላ ሳይሆን በስርአቱ የተቀጠቀጠውንና በራሱም ምክንያት በሁለንተናዊ መልኩ ደካማ የሆነውን ተቃዋሚ በመከፋፈልና በሚፈልገው ወጥመድ ውስጥ በማስገባት ነው።

ይህን ሴራ በጣጥሶ ለመውጣት የቻለው የቲም ለማ ቡድን እስካሁን ህወሃት በተለመደው ቀለበት ውስጥ ለማስገባት ያደረገውን ሙከራ እያከሸፈ ቢሄድም በተቃዋሚነት የተሰለፈው ወገን ገና ከሰመመን ያልነቃ በመሆኑ አልፎ አልፎ ዛሬም ከወጥመድ ውስጥ መላቀቅ አልቻለም። ያማ ባይሆን ኖሮ ከዶክተር አቢይ ጎን ቆሞ የጋራ የተባበረ ድምጹን ማሰማት በቻለ ነበረ። የጋራ ድምጽ ማሰማት የሚቻለው የጋራ አጀንዳ ሲኖር አይደል?

ይህም ብቻ አይደለም ተደምረናል ያሉ የኢሃዴግ ድርጅቶችም ቢሆኑ ዛሬም ችግር እንዳለባቸው ማየት ይቻላል። ይህን ታላቅ ህዝብና ሃገር በቂም ፖለቲካ ወይም በወንፈል አመራር መምራት አይቻልም ። የነዶክተር አቢይ ስልጣን ላይ መውጣት ወይም ኦፒዲ ስልጣን መያዝ ዛሬም እንደትላንቱ የህወሃት የበላይነት ወይም ሲለጠጥም የትግሬ የበላይነት እንደምንለው የኦፒዲ የበላይነት ወይም የኦሮሞ የበላይነት ስሜት እንዲፈጥር መሆን ያለበት ከሆነ ተመልሰን ዙሩ ውስጥ እንዳንገባ ጥንቃቄ ያሻል።

በዚህ ረገድ አንዳንድ የኦሮሞና የአማራ አክቲቭስቶች በሚጫወቱት የግል ሰብ እና ግንባታ ውስጥ ይንጸባረቃል። ይህ አካሄድም ለአጥፊው ጥቂት የህወሃት አመራር መሳሪያ በመሆን ለውጡን ያወሳስበዋል ። በደሞዝ የኖሩት የህወሃት አክቲቪስቶች የጥቅም ጉዳይ ነውና ልቅ አፋቸውን በከፈቱ ቁጠር የነሱን አፍ እየጠበቅን መልስ መስጠቱ ያሳንሰን እንደሁ

ነው እንጅ ከፍ አያደርገንም ። የህወሃት አክቲቭስቶች ያልኩት አሁን ቢያንስ ያለውን ለውጥ በማንኩዋሰስ የተሰለፉት በአብዛኛው እነሱ በመሆናቸው እንጂ ድንቅ አክቲቪስቶች እንዳሉ ሁሉ ሊሎች አክቲቪስቶች ሁሉ ባይከፈላቸውም የግል ስሜት ሲያጦዛቸው ከተከፈላቸው እንደማይተናነሱ በመዘንጋት አይደለም። ህዝብን ወይም አንድን ብሄር በጅምላ ከሚነክሱ ጀምሮ የህዝብ ሰቆቃን በማሳየት ብቻ አእምሮ በጎ ነገር እንዳያስብ ጥዋትና ማታ መርዝ ሲበትኑ የሚያድሩትን ማለት ነው።

በተለይም አሁን በየቦታው የምናየው ችግር መነሻ እንደምክንያት የሚቀርበው እኛው በምንረጨው መርዝመሆኑን የተረዳን አልመሰለኝም። የማንነት ጥያቄን እኛ ስናነሳው ትክክል ሊሎች ሲያነሱት ወንጀል የሚሆንበት ምክንያት አይገባኝም ። እኛ ለምንፈልጋቸው ወይም የፖለቲካ አጀንዳችንን ሊያስፈጽሙ ዪችላሉ ብለን የምናስባቸውን የማንነት ጥያቄያቸውን ለጥጠንና አጉልተን እንዲሁም የተዛባ ታሪክንም እንደመነሻ እየጠቃቀስን ሌሎች ፈጽሞ የማንነት ጥያቄ ያልነበራቸውን ህዝቦች በነዛነው መርዝ ብንመርዛቸው ሁላችንም ተጠያቂዎች መሆናችንን ማመን ተገቢ ይመስለኛል።

ባለፉት አመታት እድሜ ለህውሃት ኢሃዴግ በማንነት ጥያቄ ፖለቲካ ውስጥ ያልተዘፈቀ የህብረተሰብ ክፍል በጣም ትንሽ ነው። ይህ ደግሞ በምንም መልኩ ምክንያት እንደርድርለት እንጂ መነሻው በሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ስግብግበነት ድህነት ድንቁርና ወይም አለማወቅ ነው። የማንነት ጥያቄ ሁሉ የዚህ መገለጫ ናቸው ለማለት ሳይሆን የማንነትን ጥያቄ ለሚያነሱትም ሆነ ለሚነሳባቸው አካባቢዎች አመች የሆነ ህብረተሰብ መኖርን ይጠይቃል። እነዚህ ሶስቱ እስካሉ ድረስ ደግሞ በማንነት ስም የሚደረገው የፖለቲካ ጨዋታ ይቀጥላል።

የዶክተር አቢይ ተግዳሮቶች ዘርፈ ብዙ ናቸው። እውነት ለመናገር ከሆነ በስም የተደመሩ በግብር ግን የመደመር ጽንሰ ሃሳብ ያልገባን ብዙዎች ነን። ገና ብዙ ሊሰራበትና ሊዳብርም የሚገባው ጽንሰ ሃስብ ነው ። የሃሳቡ አመንጭ ዶከተር አቢይ ቢሆንም እንደ ህብረተሰብ ሃስቡን ማዳበር የሚገባ ይመስለኛል። ተደምረናል ስንል ዶክተር አቢይ የተናገረውን በጎ ነገር መልሶ መናገር ሳይሆን ወይም አቢይ አንድ ለማ ሁለት እኔ ሶስት እከሌ አራት..... እያልን የሂሳብ ቁጥር ማብዛት ሳይሆን የማንወዳቸውን ወይም የማይጥሙንን እንኳን ሳይቀር በሃሳብ ማቀራረብ መቻል፡ ሰጥቶ መቀበልን መለማመድ፡ ሃላፊነት የተሞላበት መልእክት ማስተላለፍ፡ ከእልህና ከቂም በቀል ነጻ የሆነ የፖለቲካ መፍትሄ ማቅረብ ፡ ከሁሉም በላይ ወደፊት የማየት ችሎታችንን ማዳበር፡ ስለ ሃገራችን ፖለቲካ ስናወሳ ስለቀበሊያችን ስለወረዳችን ስለ ክፍለሃገራችን ስለጎረቤት ሃገሮቻችን ስለአህጉራችን እንዲሁም ስለአለም ተጨባጭ ሁኔታዎች ቢያንስ መጠነኛ ግንዛቤ እንዲኖር መቻልን ያጠቃልላል።

ግሻይ ግሸ